# ይድረስ ለነጻ አውጪው ወንድሜ

እስቲ ልጠይቅህ ወንድም ዓለም?
መቼም የጥያቄ ትንሽ የለም
እባክህ
ጉዳይ አለኝ ልጠይቅህ
ፍቀድልኝ ላስቸግርህ
ያገሬ ጉዳይ ነውና የሰሞኑ ስብስብህ
እንዲገባኝ ስለምሻ ዓላማህም አካሄድህ
እባክህን ፍቀድልኝ
ጥያቄዬን መልስልኝ።
ጥያቄዬ፤
«ኢትዮጵያ»
«ኢትዮጵያዊ»
«ኢትዮጵያዊነት»
የሚሉት ስያሜዎች
የማንነት መግለጫዎች
እንዴት ሆነው ይታዩሀል?
ምንስ ትርጉም ይሰጡሀል?
ይጣፍጡሀል? ይመ–ሩሀል?
ይዋጡልሀል? ይተናነቁሀል?
ያስደስቱሀል? ያበሳጩሀል?
ያኮሩሀል? ያሳፍሩሀል?
ያሳምኑሀል? ያስክዱሀል?
ሰምቼህ ነበርና
«ተረት ናት» ስትል ትናንትና
ዛሬ . . . «ኢትዮጵያ» ስትል ግር አለኝ
የተሳሳትኩም መሰለኝ።
በእርግጥ . . . «ኢትዮጵያ» ማለትህ ደስ ይላል
«እሰዬው! እልል!» ያስብላል
ነገር ግን . . . ስቃኘው የዓለምን ሁኔታ
ስከታተለው ጠዋት ማታ
አልተለያትም ላንዳፍታ
የፖለቲካ ቁማር፥ የድርድር ጨዋታ።
ዓላማን ግብ ለማድረስ
        የራስን ጥቅም ለማስጠበቅ
ያልሆኑትን ሆኖ መቅረብ
        የእስስትነት ባሕርይ ማጥለቅ
በመወዳጀት ታክቲክ ሰበብ
        በግንባር ፈጠራ ሂደት
በ«ጠላቴ ጠላት» መርህ
        ድል እንደሚሸምቱበት
አውቃለሁ . . .
አንዳንዴም ደግሞ
        እንደ ብልሹ ነውረኛ
ፖለቲካ ዐይን አውጣ ነው
        ከማንም ጋር የሚያስተኛ።
ቢሆንም . . .
የትናንትናውን ሽፋፍነህ
        ዛሬ «ኢትዮጵያ» ብትለኝ
ጠልተሀት ነበርና ከቶ አልዋጥልህ አለኝ።
እስቲ ልጠይቅህ ወንድምዬ . . .
በየዓለማቱ አደባባይ እንደባላንጣ የከሰስካት
እናትህ ሆና ሳለች ልጅነትህን የካድካት

ባጎረሰችሀ የነከሰካት
ባሳደገችህ የረገጥካት
አፍሪካዊ ክብርዋን ንቀህ በታሪክዋ ያሾፍክባት
ያወረሰችህን ክቡር ፊደል በፈረንጅ ሆሄ የፋቅክባት
በቅኝ ገዢ የመሰልካት
እንደ ወንጀለኛ ያሳደድካት
እንደ ውዳቂ ያጣጣልካት
ስምዋን መጥራት እስኪቀፍህ
         የውርደት ጭቃ የቀባሀት
ለመገንጠል ያሤርክባት
ለማጥፋት ያደምክባት
ልትበታትን ያጠቃሀት
አንተነትህን ቀይረህ እሱዋነትዋን የነፈግሀት
እስቲ ልጠይቅህ ንገረኝ
         ኢትዮጵያ ላንተ ምንድናት?
ምንድናት ላንተ ኢትዮጵያ
         ኢትዮጵያዊነትስ ምንድነው?
እርግማን ነው ብለህ ነበር
         የነገርከኝን ሳስታውሰው
እውነት ስለእውነት
ምንድነው ላንተ ኢትዮጵያዊነት?
ነጻነት?
ባርነት?
ላንተ . . . ምንድነው ኢትዮጵያዊነት?
በምእተ ዓመታት ታሪክ
         በአገር ግንባታ ሂደት
ተቀራርቦ ተለማምዶ
         አብሮ ችግር ሲወርድበት
በአንድነት የኖረን ሕዝብ ልዩነቱን አቻችሎ
ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን ከወራሪ ተከላክሎ . . .
ነጻ ካላወጣሁህ ስትለው
ከማንነቱ ልትለያየው
ከኢትዮጵያዊነቱ አፋትተህ
         የቅዠት ዒላማህ ልታደርገው
ስትደክም አይቻለሁና
እስቲ አስረዳኝ በጽሞና።
የትናንትናው መንገድህ
         የዛሬውን እያስፈራኝ
ልጠርጥርህ? ላመስግንህ?
         ግራ ብጋባ አትጥላኝ።
አፍህን ሞልተህ በሙሉ ልብ
         «የኢትዮጵያ ልጅ ነኝ» በለኝና
የወያኔን «እስከመገንጠል»
         እንሰርዘው እንበርታና።
እስቲ ልስማው ካንደበትህ «ኢትዮጵያ» የሚለውን ስም
ከጎንህ እንድሰለፍ በርታ እንድልህ የኔ ወንድም።
አዎ . . . ወንድሜ ነህ ወንድምህ ነኝ
ግን . . . ስለ ኢትዮጵያ ብለህ የእምነት ቃልህን ስጠኝ
አብረን እንድንገነባት
የበደልናትን እንድንክሳት
እባክህ አስረዳኝ ስለእውነት . . . ስለእናት
«ኢትዮጵያ» ላንተ ምንድናት?

---

**ቴዎድሮስ አበበ**
May 24, 2006